# የፌደራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

## የመጀመሪያ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባት የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ

ጥቅምት 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ



Scanned with CamScanner

## መመሪያ ቁጥር 17/2013

# የሁሉም የመንግሥትና የግል የአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባትን በአዲስ መልክ ለማቋቋምና ለማደራጀት የወጣ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ

ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጆች ድረስ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎችን በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ከመቅረጽ ባሻገር ተማሪዎች በመልካም ሥነ ምግባር ተገንብተውና ጥሩ ስብእናን ተላብሰው እንዲያድጉ ማስቻል ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡ ወደፊት ከሙስና፣ ከብልሹ አሰራርና ከኋላቀርነት የተላቀቀች፣ በዕድገት ጎዳና የምትገዝና ለዜጎቿ ምቹ የሆነች ኢትዮጵያን ለማየት ዛሬ በትውልድ ሥነ ምግባርና ስብእና ግንባታ ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡ የሥነ ምግባር ግንባታ ተግባር የሚጀምረውና ጽንዑ መሠረቱ የሚጣለው በልጅነትና በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ በመሆኑ ለዚህ ተግባር ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራቱ ተገቢ በመሆኑ፣

ይህንን አገራዊ ግብ ለማሳካት ተማሪዎች ሰፊ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉባቸው የትምህርት ተቋማት ተመራጭ እንደሆኑ ከታመነበት ደግሞ ሥራውን ለማሳለጥ የሚያስችል አደረጃጀት በሁሉም መደበኛ በሆኑ የትምህርት እርከኖች መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በፊት ሚያዝያ 1996 ዓ.ም በፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና በትምህርት ሚኒስቴር ትብብር በተደረሰው ስምምነት መሠረት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የሥነ ዜጋና እና ሥነ ምግባር ክበባት የአደረጃጀት መመሪያ መዘጋጀቱ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ አሰራሩ ሁለት ውስንነቶች የነበሩበት በመሆኑ፣

አንደኛው በመንግሥት ት/ቤቶች በተወሰኑ የትምህርት እርከኖች ላይ ብቻ ማተኮሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተማሪዎች የሥነ ምግባር ጉዳይ ከሌላ ትምህርት ዓለም ጋር የተገናኘና ኩረጃ፣ ስርቆት፣ የመሳሰሉት ኢሥነ ምግባዊ ድርጊቶችን ወደ ጎን የተወ ነበር፡፡ ስለሆነም ኮሚሽኑ የአደረጃጀት ወሰኑን በማስፋትና ክበቡን ራሱን በማስቻል ተልዕኮ ተኮር አድርጎ ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም በመንግሥት የተሰጠውን ህጻናትና ወጣቶችን በመልካም ሥነ ምግባር የመገንባት ህጋዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከትምህርት



Scanned with CamScanner

ሚኒስቴር ጋር በመተናጀት በሁሉም የአንደኛ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባትን በማቋቋም ወደ ሥራ መግባት የሚያስፈልግ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/1997(አዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 30(2) መሰረት ይህ የሁሉም የመንግሥትና የግል የአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች ተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባትን በአዲስ መልክ ለማቋቋምና ለማደራጀት ይህ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ወጥቷል።



Scanned with CamScanner

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የአንደኛ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 17/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2.

ትርጓሜ

1. "ክበብ" ማለት የአንደኛ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ ማለት ነው፡፡
2. "አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" በትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና አግኝቶ በሥርዓተ ትምህርት የተቀመጠውን ትምህርት ከ1ኛ እስከ 8ኛ የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የሚያስተምር የመንግስት ወይም የግል ትምህርት ቤት ማለት ነው፡፡
3. ‹‹ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" በትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና አግኝቶ በሥርዓተ ትምህርት የተቀመጠውን ትምህርት ከ9ኛ እስከ 12ኛ የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የሚያስተምር የመንግስት ወይም የግል ትምህርት ቤት ማለት ነው፡፡
4. "ኮሌጅ" በትምህርት ሚኒስቴር ህጋዊ ዕውቅና አግኝቶ በሥርዓተ ትምህርት የተቀመጠውን ትምህርት በመምህራን ትምህርት፣ በጤና ሳይንስ፣ በቴክኒክና ሙያ፣ በግብርና እና በመሳሰሉት ከሊጆች በተለያየ የሙያ መስኮች ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያሰለጥን የመንግስት ወይም የግል የትምህርት ተቋም ማለት ነው፡፡
5. "የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ" ማለት በተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ መሰረተ መልካም እሴቶችን ለማጎልበት፣ ይህንን የሚፃረሩ ኩረጃ፣ ስንፍናና ስርቆት የመሳሰሉትን ኢ-ሥነ ምግባራዊ ድርጊቶችን ለመከላከል ዓላማ ያደረገ በግልና በመንግሥት በአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በኮሌጆች የተቋቋሙ ክበባት ማለት ነው፡፡



Scanned with CamScanner

በክህሎትና በአመለካከት የዳበረ ብቁ ዜጋ በመልካም ሥነምግባር ለመገንባትና የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው። ከዚህ በተጨማሪ መመሪያው የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎችን ያካትታል፡-

1. በተማሪዎችና በመማር ማስተማሩ ዙሪያ የሚታዩ ኩረጃ፣ ስንፍና፣ ስርቆት አድሎአዊ አሰራሮችን በማስወገድ በራስ ጥረት የሚያድግ ሥነ ምግባርን ማጎልበት፣
2. የተማሪዎች አጠቃላይ መልካም ሥነ ምግባርና ስብእና የሚያጎለብቱ እና ሙስናን የሚያወግዙ ስራዎችን በልዩ ትኩረት ለማከናወን፣
3. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ግንባታን በማጠናከር በራስ ጥረት የመለወጥ ብቃት የሚያጎናጽፍ አትም ያለው ተማሪ ለመፍጠር፣
4. ተማሪዎች በመልካም ሥነ ምግባር እንዲገነቡ እና ሙስናን እንዲፀየፉ የማድረግ ስራ በመሥራት መልካም ሥነ ምግባር የተላበሰ ትውልድ የማረጋገጥ ሥራ በትምህርት ቤት ተቋማዊ ጎልውና ኖሮት ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ፣
5. ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው እንዲሁም ከመምህራንና ከአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመልካም ሥነምግባር እሴቶች ላይ የተመሠረተ ለማድረግና በሁሉም የተቀናጀ ሥራ ለማስፈጸም፣

## ክፍል ሁለት
## አባልነት፣ የአባልነት መብትና ግዴታ

### አንቀፅ 6
### ስለ አባልነት

1. ሁሉም የትምህርት ተቋሙ ተማሪዎች የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ አባል ይሆናሉ፣
2. ሁሉም የክበቡ አባላት የክበቡን ዓላማ ተቀብለው በፈቃደኝነት፣ በፍላጎት እና በተነሳሽነት እንዲሰሩ ይጠበቃል፣
3. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ አስተባባሪ ከ5-7 አባላት ይኖሩታል።

### አንቀጽ 7
### የአባላት መብት

1. ሁሉም የክበቡ አባላት እኩል መብት አላቸው፣
2. ማንኛውም የክበቡ አባል፡-



Scanned with CamScanner

2.1. ለክበቡ ዓላማና ተልዕኮ መሳካት የሚጠቅሙና የክበቡን አሰራር የተከተሉ ማናቸውንም ዓይነት ስራ የመስራት፣

2.2. በኃላፊነት የመመረጥ፣ የመምረጥና የክበቡን እንቅስቃሴ በተመለከተ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣

2.3. ስለክበቡ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምፅ የመስጠት፣

2.4. ክበቡ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብቶችች አሉት።

አንቀጽ 8

የአባላት ግዴታ

ማንኛውም አባል በመመሪያው የተቀመጡትን ግዴታዎች ማክበር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የክበቡን ዓላማ ለማሳካት የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት፣
2. የትምህርት ቤቱ እና የክበቡን ንብረት መጠበቅና የመንከባከብ፣
3. የክበቡን መተዳደሪያ መመሪያ፣ የክበቡን አስተባባሪዎች ውሳኔዎችን ማክበርና የመፈፀም፣
4. በክበቡ መደበኛና አስቸኳይ የመወያያ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት፣
5. የክበቡን አቅም ለማጎልበት፣ ዓላማውን ለማሳካትና ለማስፋፋት በሀሳብ፣ በጉልበት፣ ወዘተ የመደገፍ
6. ራስን ከኩረጃ፣ ከስርቆት፣ እና ከሌሎች ኢ-ሥነ ምግባራዊ ድርጊቶች የማጽዳት፣
7. የመንግሥት ሀብትና ንብረትን የመጠበቅ፣ ኢ-ሥነ ምግባራዊ ድርጊቶችና ብልሹ አሰራሮች ተፈጽመው ሲመለከት ጥቆማ የመስጠት፤
8. የተቋሙን ሀብት ከብክነት የመከላከልና ሙስናን የመታገል ግዴታ አለበት፣

አንቀጽ 9

ስለአባልነት ዘመን

9.1. ከአባልነት ስለመውጣት

ማንኛውም የክበቡ አባል ከክበቡ አባልነት የሚወጣው በትምህርት ተቋሙ የሚቆይበት የትምህርት ዘመንን ሲያጠናቅቅ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ይሆናል፣



Scanned with CamScanner

9.2. አባሉን ከፍተኛ ተግሳጽ የሚያስጡ ድርጊቶች

1. የክበቡን ተቀባይነትና አርአያነት የሚያጎድፍ ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት በተደጋጋሚ ፈጽሞ ሲገኝ እና በማስረጃ ሲረጋገጥ ፤
2. የክበቡን የስራ ሂደት የሚያውክና ስም የሚያጎድፍ፣ ያለአስተባባሪው ፈቃድ ክበቡን የግል ጉዳዩ ማስፈጸሚያ እንደተጠቀመበት በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
3. በመመሪያው የተቀመጡ አሰራሮችን ሆን ብሎ/ በግዴለሽነት/ መጣሱ ወይም መመሪያውን የሚጥስ ተግባር መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣
4. አባሉ በመመሪያው የተቀመጡትን ግዴታዎች ያልተወጣና ለመወጣትም ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፣
5. ክበቡ በሚጠራቸው ስብሰባዎች ከዓቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ለ3 ተከታታይ ጊዜ ያስፈቃድ ሲቀር ከፍ ያለ ተግሳጽ ምክር ይሰጠዋል፣

## ክፍል ሶስት

## አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

### አንቀጽ 10

### የክበቡ አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ወይም ኮሌጁ ለሚመደበው ክበቡን ለሚከታተል አካል(focal person) ነው፡፡
2. ክበቡ እንደ የተቋማቱ ባህርይ የሚደራጅ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡፡






አንቀጽ 11

**የክበቡ አስተባባሪ አባላት**

የክበቡ አስተባባሪ አባላት ብዛት እንደየትምህርት ቤቱና ኮሌጁ ባህርይ የሚወሰን ሆኖ ከ5-7 አባላት የሚኖሩት ይሆናል፡፡ ሰባት አስተባባሪ ለሚኖራቸው ክበባት የሚከተሉት አባላት የሚኖራቸው ይሆናል፡፡

1. ሰብሳቢ
2. ምክትል ሰብሳቢ
3. ፀሐፊ
4. የአባላት ጉዳይ ክትትል ተጠሪ
5. ሥነ ምግባርና የብልሹ አሰራር ክትትል ተጠሪ
6. የህዝብ ግንኙነት ተጠሪ/
7. የሴት ተማሪዎች ጉዳይ ተጠሪ

**አንቀጽ 12**

**የትምህርት ተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት**

**ሀ. የትምህርት ቤቱ/ ኮሌጁ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት**

1. ክበቡን በሚመለከት ከትምህርት ሚኒስቴር እና በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት ፅ/ቤቶች የሚወርዱ አቅጣጫዎችን ተከትሎ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ያደራጃል፣ ወደ ተግባር እንዲገባ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ ስራ በዓመታዊ የትምህርት ቤቱ እቅድ ላይ እንዲካተት፣ እንዲታቀድ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣



Scanned with CamScanner

4. ክበቡ ለሚያከናውናቸው ስራዎች በጀት ይመድባል፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

5. ለክበቡ አመራሮች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ይመድባል፤

6. ክበቡ ቢሮ እንዲኖረውና ለስራ አመች የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

7. ኩረጃን፣ ስርቆትን፣ ማታለልን፣ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ውጤት ከአስመዘገቡ ክበቦች ተቋማት ክበባት የተሻለ ተሞክሮ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎች እንዲሸፈኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

8. ክበቡ ሊደግፉ የሚችሉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመለየትና ግንኙነት መፍጠር ክበቡን እንዲደግፉ ያሳምናል፤

9. የትምህርት ተቋሙ የክበባት መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፤

10. የእቅድ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ይደግፋል፣

11. የትምህርት ቤቱ/ ኮሌጁ መምህራንና ሠራተኞች ለክበቡ አባላትና ለተማሪዎቻቸው በመልካም ሥነ ምግባር አርአያ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋል፣

12. ከፍተኛ የሆነ የሥነ ምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት እንዲስተካከሉ አርአያነት ባላቸው መምህራን እንዲመከሩ ያደርጋል፣

13. በተማሪዎች ላይ ያልተገባ ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት የሚፈፅሙ መምህራን እንዲለዩ እንዲታረሙ እና ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

14. በትምህርት ተቋሙ ውስጥ ለተማሪዎች ሥነ ምግባር መጓደል ምክንያት የሆኑ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት እንዲፈቱ ሙያዊ እገዛ ያደርጋል፣

15. ለተማሪዎች ሥነ ምግባር ግንባታ የሚያግዙ የማስተማሪያ ጽሁፎች እንዲዘጋጁ፣ ሥልጠና እንዲሰጡ መምህራንን ያበረታታል፣ይደግፋል፣



Scanned with CamScanner

ለ. የትምህርት ቤቱ/ኮሌጁ የክበባት ጉዳይ ፎካል ፐርሰን ተግባርና ኃላፊነት

1. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብን ኃላፊነት ወስዶ ያደራጃል፣ይደግፋል፣ ይከታተላል፣
2. የክበቡ አባላት በተሰጣቸው ዓላማና አሠራር መሠረት እንዲንቀሳቀሱ ምክር እና ድጋፍ ይሰጣል፤
3. የትምህርት ቤቱ እና የኮሌጁ ማኅበረሰብ ለክበቡ ድጋፍና ትብብር እንዲያደርግ የግንኙነት ማእከል ሆኖ ያገለግላል፣
4. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ግንባታ በክበቡና በትምህርት ቤቱ/ኮሌጁ የተለያዩ የስራ ክፍሎችና በመምህራን በተቀናጀ መንገድ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
5. ክበቡ ለሚያከናዉናቸው ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ የበጀት፣ የቢሮ፣ የቁሳቁስ እንዲሁም የአዳራሽ ፍላጎቶች እንዲሟሉ በዓመታዊ እቅዱ በጀት በማስያዝ ወይም በትምህርት ተቋሙ በበላይ ኃላፊዎችን በማሳመን እንዲሟሉ ያደርጋል።
6. በኮሚሽኖችና ሌሎች አጋር ድርጅቶች በሚዘጋጁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ላይ የክበቡ አመራሮችና አባላት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
7. ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በትምህርት ተቋሙ በስፋት እንዲከበር የማስተባበር እና የመደገፍ ሥራዎችን ያከናውናል፣
8. የክበቡን አስተባባሪዎችና አባላትን የአቅም ክፍተት በመለየት አማራጭ መፍትሔዎችን ያስቀምጣል፣ ይተገብራል፣
9. የክበቡ አባላትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይተገብራል፣ አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ያደርጋል
10. ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚያጋልጡ እና የሚጠቁሙ ተማሪዎችን ያበረታታል ፤
11. የክበቡን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በክበቡ አመራርና አባላት ተሳትፎ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣፣
12. የክበቡን ዓመታዊ እቅድ ያፀድቃል፣ ተፈፃሚነቱን ይገመግማል፣
13. የክበቡን ዓመታዊ እቅድ፣ የየሩብ እና የግማሽ ዓመት ሪፖርት ለወረዳ ሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ወይም ይህን ስራ እንዲከታተል የወረዳው ትምህርት ፅ/ቤት ለሚመደበው አካል ሪፖርት ይልካል፣



Scanned with CamScanner

1. በየደረጃው መረጃ ይሰበስባሉ ፤ ሪፖርት አጠናቅረው ተጠሪ ለሆኑለት አካል ይልካሉ፤ በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ተፈፃሚነቱን ይከታተላሉ፣

2. በየደረጃው የወረደላቸውን የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባት መሪ እቅድ ወደ ታችኛው መዋቅር ያወርዳሉ፤ ኦሬንቴሽን ይሰጣሉ፤ አፈፃፀሙ ይከታተላሉ፣

3. በየደረጃቸው የሚገኙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ እና እገዛ ያደርጋሉ፣

4. በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት ፅ/ቤት እና የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ግንኙነት ይፈጥራሉ ፤ በቅንጅት ይሰራሉ፣

5. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባት የፋይናንስ እና ዓቅም ግንባታ ድጋፍ እንድያገኙ በየደረጃው ከሚገኙ አካላት ጋር በጋራ ይሰራሉ፣

6. የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባት በሥነ ምግባር ግንባር ሥራ ላይ ጠንካራ ሆነው እንዲወጡ የአማካሪ ሚና ይጫወታሉ ፤

7. በተቀመጠው የግንኙነት ጊዜ መሰረት የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበባት እንቅስቃሴ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በጋራ ይገመግማሉ፤ አፈፃፀሙን ይከታተላሉ፣

8. ጠንካራ የሪፖርት እና የግንኙት ሥርዓት በየደረጃው እንዲፈጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤

## አንቀጽ 15

## የክበቡ ተግባርና ኃላፊነት

1. የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ክበቡ በመልካም ሥነ ምግባር ግንባታ ዙሪያ የሚሰጠውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያስተዋውቃል፣
2. በተማሪዎች ሥነ ምግባር ግንባታ ስትራተጂ እንዲፈፀሙ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ይተገብራል፣
3. የተማሪዎች ሥነ-ምግባር ግንባታ የሚያሳድጉ ሌሎች ተግባራትን ለይቶ ያቅዳል፣ ይፈጽማል፣



Scanned with CamScanner

1. የክበቡን ስብሰባዎች በበላይነት ይመራል፤
2. የክበቡ አስተባባሪዎች ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤
3. በክበቡ እንዲፈፀሙ የታቀዱ ተግባራትን አፈፃፀም ይከታተላል፤
4. የክበቡ መመሪያ ተፈፃሚነትን ይከታተላል፤
5. የክበቡ አባላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፤ እገዛ ያደርጋል፤
6. ክበቡን ወክሎ ከሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤
7. በክበቡ ስር የሚዋቀሩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤
8. በክበቡ አባላት የታመነባቸውን ሌሎች ተግባራትን ያስፈፅማል።

አንቀጽ 18

**የክበቡ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

ምክትል ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለሰብሳቢው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. የክበቡን ንዑሳን ተጠሪዎች በበላይነት ይመራል፤
2. ከሰብሳቢውና ከፀሐፊው ጋር በመሆን ለክበቡ አስተባባሪዎች የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤
3. ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
4. በሰብሳቢው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን በተጨማሪነት ያከናውናል።

አንቀጽ 19

**የክበቡ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት**

1. በክበቡ የሚካሄዱ ስበሰባዎችን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤ ያደራጃል፤
2. የክበቡን የአስተዳደር፣ የጽህፈትና የፋይል መዛግብትን በኃላፊነት ይይዛል፤
3. ከሰብሳቢውና ከም/ሰብሳቢው ጋር በመሆን ለክበቡ አስተባባሪዎች የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤
4. በክበቡ የተሰሩ ስራዎች መነሻ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሰብሳቢውና ለአስተባባሪዎች ያቀርባል፤
5. የክበቡን የፅሁፍ ስራዎች ያከናውናል እንዲሁም ደብዳቤዎችን፣ ሰነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን በአግባቡ ሰንዶ ይይዛል፤



Scanned with CamScanner

6. በክበቡ አስተባባሪዎች የተወሰኑ ውሳኔዎች፣ የተሰጡ መልእክቶች በተደራጀ ሁኔታ ለአባላትና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያደርሳል፣
7. በተለያዩ አካላት የሚሰጡ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፎችን አጠቃቀም በተመልከተ ክትትል ያደርጋል፣
8. በሰብሳቢው የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን በተጨማሪነት ያከናውናል።

አንቀጽ 20

**የክበቡ የአባላት ጉዳይ ክትትል ተጠሪ**

የክበቡ የአባላት ጉዳይ ክትትል ተጠሪነቱ ለሰብሳቢው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1. የክበቡ የአባላት ጉዳይ ስራን በበላይነት ይመራል ፤ ያስተባብራል ፤
2. የክበቡ አባላት መረጃ ያደራጃል፣ በአግባቡ ይይዛል፣
3. የክበቡ የአባላት ጉዳይ ክትትልን እቅድ ያዘጋጃል ፤ ተፈፃሚነት ይከታተላል
4. በክበቡ የአሰራር መመሪያ መሠረት በአዳዲስ አባላት እንዲጠናከር ያደርጋል ፤ ስለክበቡ ዓላማና አሰራር በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ገለጻ ይሰጣል፣
5. ለክበቡ አባላትና ተማሪዎች ሥነምግባር ግንባታ የሚረዱ የሥልጠና ርእሶችን ከክበቡ አስተባባሪዎች ጋር በመሆን ይለያል፣ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
6. በክበቡ ተግባርና ኃላፊነት የተቀመጡ ሌሎች የስነ ምግባር ግንባታ ስራዎች ያከናውናል፣
7. እንደ ትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ብዛት የክበቡ ተወካይ በሴክሽንና በክፍል ደረጃ እንዲወከል ያደርጋል፣
8. የከፍሉን አፈፃፀም ይገመግማል ፤ ሪፖርት ለሰብሳቢ ይልካል ፤
9. ከሰብሳቢው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፡፡

አንቀጽ 21

**የክበቡ ሥነ ምግባርና የብልሹ አሰራር ክትትል ተጠሪ ተግባርና ኃላፊነት**

1. የሥነ ምግባር ጉድለትን፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የጥቆማ መቀበያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ጥቆማን ይቀበላል፣
2. የቀረቡ ጥቆማዎችን ያጣራል፣ ለክበቡ አስተባባሪዎች በማቅረብ ለውሳኔ ለክበቡ ፎካል ፐርሰን ያቀርባል፣ ውሳኔ መሰጠቱን ይከታተላል፣



Scanned with CamScanner

9. የዘ[illegible] የስራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ሪፖርት ለስብሰባው ይልካል፣
10. ሌሎች በስብሰባዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

## ክፍል አራት

## የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ አሰራር

በዚህ መመሪያ ሌሎች አንቀፆች የተደነገጉ አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነዉ ክበቡ የሚከተሉት አሰራሮች ይኖሩታል።

### አንቀፅ 24

### የክበቡ አስተባባሪዎች መምረጫ መስፈርት

የክበቡ አባል የሆነና ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ አባል ከሁሉቱም ፆታዎች በክበቡ አስተባባሪ አባል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል፦

1. ክበቡ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ሙሉ እምነት፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያለው፣
2. በተቋቋመዉ የተማሪዎች የሥነ ምግባር ክበብ እንቅስቃሴ ንቁ ተሳታፊ የሆነ፣
3. በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና በክበቡ አባላት ዘንድ በመልካም ሥነምግባሩ አርአያ የሆነና ተቀባይነት ያለው፣
4. የክበቡን ደንብና ስርዓት አክብሮ የሚንቀሳቀስ ፣
5. በትምህርት ተቋሙ ውስጥ በሚደረግ ፀረ ሙስና እንቅስቃሴ በመሳተፍ የማስተባበር እና የመምራት አቅም ያለው፣

### አንቀጽ 25

### የክበቡ ድምፅ አሰጣጥ

1. በማንኛውም ስብሰባ ውሳኔ ሲተላለፍ አንድ አባል አንድ ድምፅ ይኖረዋል፣
2. የክበቡ አስተባባሪ አባላት ምርጫ እንደአስፈላጊነቱ በግልፅ ወይም በምስጢር የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ይከናወናል፣

### አንቀጽ 26

### የአባል አቀባበል ስርዓት

1. ማንኛውም አባል የሆነ ተማሪ አባል ለመሆን በቃል ወይም በፅሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ፣



Scanned with CamScanner

2. ሁሉም ተማሪዎች የክበቡ አባል እንዲሆኑ በክበቡ የህዝብ ግንኙነት በኩል የማሳመን ሥራ በመስራት፣
3. የክበቡ አባል ለማብዛት የሚያግዙ የተለያዩ ዜዴዎች በመጠቀም ሰፋፊ ቅስቀሳ በማድረግ፣

## ክፍል አምስት

## ስለ ግንኙነት ስርዓት

### አንቀጽ 27

### የሥነ ምግባር ክበብ ከአጋዥ ድርጅቶች ጋር ስለሚኖረዉ ግንኙነት

የክበቡን ዓላማና ተግባር ለማደግፉ ወይም ድጋፍ ለማድርግ ከሚፈልጉ እና በሥነምግባር ጉዳይ ላይ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ትብብር ሊያደርግ ይችላል፣

### አንቀጽ 28

### ክበቡ ከትምህርት ተቋሙና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ስለሚኖረዉ ግንኙነት

1. ክበቡ ከትምህርት ተቋሙ አመራር የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ ጽ/ቤት እና የመስሪያ ቁሳቁስ ለማግኘት በሚደረግ ጥረት የሥራ ግንኙነት ይኖራል።
2. ክበቡ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በመልካም ሥነምግባር ለማነፅ፣ ሙስናን፣ ብልሹና አድሎአዊ አሰራሮችን በጋራ ለመዋጋትና ለመታገል በትብብር ሊሰሩ ይችላሉ፣፣
3. ክበቡ ከህብረተሰቡ የተለያዩ ድጋፎችን ሲፈልግ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም በሚመለከተው ክፍል/አካል ፈቃድ ሲያገኝ ህብረተሰቡን ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ ማስገደድ ወይም ጫና መፍጠር ግን የተከለከለ ነዉ።

### አንቀጽ 29

### ክበቡ ከኮሚሽኑ ጋር ስለሚኖር የስራ ግንኙነት እና ድጋፍን በተመለከተ

1. አስተባባሪዎች ተዋረዱን ጠብቀው በማንኛውም ጊዜ እና ጉዳይ ኮሚሽኑን ምክር መጠየቅ ይችላሉ፣
2. ኮሚሽኑ ባፀደቀው የአሰራር እና የአደረጃጀት መመሪያ መሰረት በዕቅድ፣ ሪፖርት እና ከሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል ፣



Scanned with CamScanner

3. በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት ፅ/ቤት ጋር በመቀናጀት የክበባት አመራሮችና አባላትን ሰማስልጠንና ሰማብቃት የሥራ ግንኙነት ይኖራል፣
4. ክበባቱ በአሰራራቸው ላይ ችግር ሲያጋጥማቸው ተዋረዱን ጠብቆ ችግሩ እንዲፈታ እገዛ ያደርጋል፣
5. እርስ በርስ ልምድ የሚለዋወጡበት መድረክ ያዘጋጃል፣
6. ጥሩ ልምድ ያላቸውን ክበባት ልምድ በመቀመር ለሌሎች እንዲተላለፍ ያደርጋል፣
7. ተዋረዱን ጠብቆ አትድና ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
8. ጥሩ የሰሩትን ያበረታታል፣ በኮሚሽኑ የሽልማት መመሪያ መሰረት ይሸልማል ::

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 30

### ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

### አንቀጽ 31

### መመሪያውን ስለማሻሻል

1. ይህ መመሪያ በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን እንዲሻሻል የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ የሚሻሻል ይሆናል ::
2. ትምህርት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፣ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፤



Scanned with CamScanner

አንቀጽ 32

መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ የአደረጃጀት እና የአሰራር መመሪያ ከጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፤ ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም

ፀጋ አራጌ

የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር



Scanned with CamScanner